የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ሀገር አቀፍ ቅድመ-ሆስፒታል ድንገተኛ ህክምና እና

# የአምቡላንስ

# አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ




2006 ዓ.ም

## መቅድም

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር የሀገሪቷን ጤና ስርዓት ለማሻሻልና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማዳረስ ቀዳሚውን ድርሻ ይዞ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ይገኛል ፡፡ከዚህም ውስጥ የድንገተኛ ህክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት እንደዋንኛው የሚኒስቴሩ ግብ በመውሰድ ከዚህ ቀደም ከከተማ ከንቲባዎችና ከክልል ፕሬዝዳንቶች ጋር ስለአምቡላንስ አጠቃቀም ላይ የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ከአንድ ሺህ (1000) የሚበልጡ አምቡላንሶችን ገዝቶ አሰራጭቶዋል ፡፡

እነዚህ አምቡላንሶችም በ2015 ዓ.ም የሚጠናቀቀውን የምእተአመቱ ግብ የሆነው የእናቶችንና የህጻናትን ሞት ለመቀንስ አይነተኛ መፍትሄ እንዳለው በማሰብ በሀገሪቱ ላሉ ለሁሉም ወረዳዎች እንዲዳረስ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም አምቡላንሶቹ ማናቸውንም ድንገተኛ ህመም የተፈጥሮ ሆነ ሰውሰራሽ አደጋ ላጋጠማቸው ዜጎች የህይወት አድን እርዳታ እየሰጠ ዘላቂ ህክምና ወደሚያገኙበት ጤና ተቋም እንዲያደርስ የታለመለት ሲሆን ይህንንም በሰለጠኑ ባለሙያተኞች የታገዘ ለማድረግ የአምቡላንስ ውስጥ ባለሙያተኞች(Emergency medical technician) በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እያሰለጠነ ይገኛል ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶችን በጥራትና ወጥነት ባለው መልኩ ለማካሄድ ይህ ሀገር አቀፍ የቅድመ ሆስፒታል ድንገተኛ ህክምና የአምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ሁሉም የሚመለከታችው አካላት እንዲተገብሩት የሚገባ ነው፡፡መመሪያው በድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልገሎት አወቃቀርና ፍሰት፣ በባለድርሻ አካላት ሀላፊነት እንዲሁም በሰውሀይል አስተዳደር እና በድጋፍና ክትትል ሂደት ላይ ትኩረት እየሰጠ ሲሆን በየደረጃው ያሉ የስራ ሀላፊዎችና በአምቡላንስ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ሀላፊነታቸውና ተጠያቂነታቸውን ለመወጣት የሚያግዝ መፀሐፍ ነው፡፡

ይህን እድል ተጠቅሜ ለዚህ መመሪያ ዝግጅት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ዶ/ር ሄለና ሀይሉ

## ምስጋና


የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከታች የተዘረዘሩትን ባለሙያዎችና መስሪያ ቤታቸውን ለዚህ የድንገተኛና አመቡላንስ መመሪያ ዝግጅት ላይ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ምስጋናውን ያቀርባል ፡፡

| ስም | የሚሰሩበት ተቋም |
|---|---|
| 1. ዶ/ር አብረሀም እንደሻው | ጤና ጥበቃ ሚ/ር ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| 2. አቶ አብረሀም ዘለቀ ዘወልዴ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 3. አቶ ያቆብ ሰማን | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 4. አቶ ጌትነት ደስታ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት |
| 5. አቶ አሰግድ ሳሙኤል | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣የሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት |
| 6. አቶ ረጋሳ ባይሳ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 7. ዶ/ር ሔለና ኃይሉ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 8. አቶ ቀሬ ነገያ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 9. ወ/ሮ ጤናዬ ደምሴ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 10. አቶ አለማየሁ ብርሀኑ | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 11. አቶ በሀይሉ ተ/ማሪያም | ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ሜዲካል አገልሎት ዳይሬክቶሬት |
| 12. ዶ/ር አሰፉ ወ/ዓዲቅ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| 13. ዶ/ር ፍኖት ደበበ | ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆ/ል |
| 14. አቶ ንጉሴ ሲሳይ | የኢትዮጲያ ቀይ መስቀል ማሕበር |
| 15. አቶ ኢዮቤድ ካሌብ | አዲስ አበባ ጤና ቢሮ |
| 16. አቶ ሀይማኖት ገረመው | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| 17. አቶ ልኡልሰገድ አህመድ | ክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢኒሼቲቭ |
| 18. አቶ አበባው ደርሶ | ክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢኒሼቲቭ |
| 19. አቶ ዳዊት ዱጉማ | እ/ድ/አ/መ/መ/ኤጀንሲ |
| 20. አቶ ይታገስ መንግስቱ | ጠብታ አምቡላንስ |
| 21. ሲ/ር ዓለም ታደሰ | እ/ድ/አ/መ/መ/ኤጀንሲ |

## ማውጫ

ምስጋና....................................................................................................2

1. መግቢያ ....................................................................................................5

2. የመመሪያው አስፈላጊነት..........................................................................7

3. ዓላማ....................................................................................................7

3.1 ዋና ዓላማ....................................................................................................7

3.2 ዝርዝር ዓላማዎች....................................................................................................7

4. ኦፐሬሽናል ስታንደርድ..........................................................................8

5. የመመሪያው ተፈጻሚነት ..........................................................................8

6. መዋቅርና አስተዳደር ..........................................................................9

7. የአምቡላንስና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ፍሰት ..................................13

8. የባለ ድርሻ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት ..................................................15

8.1 የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ሀላፊነት.......................................15

8.2 የክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ..........................................................16

8.3 የክልል ጤና ቢሮዎች ተግባርና ሀላፊነት ..................................................17

8.4 የዞን ጤና ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት ..........................................................18

8.5 የወረዳ መስተዳድር ተግባርና ሀላፊነት..........................................................18

8.6 የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት..........................................................19

8.7 የጥሪ መቀበያ ማእከል ሰራተኛ ተግባርና ሀላፊነት.......................................20

8.8 የጤና ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት ..........................................................20

8.9 የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያን ተግባርና ሀላፊነት.......................................21

8.10 የአምቡላንስ ሹፌር ተግባርና ሀላፊነት ..........................................................22

8.11 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙዎች ተግባርና ሀላፊነት.......................................22

8.12 የህብረተሰቡ ተግባርና ሀላፊነት ..........................................................22

8.13 የፖሊስ ተግባርና ሀላፊነት..........................................................23

8.14 የትራፊክ ፖሊስ ተግባርና ሀላፊነት..........................................................23

8.15 የኢትዮጲያ ቀይ መስቀል ማህበር ተግባርና ሀላፊነት.......................................24

8.16 የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ኤጀንሲ ተግባርና ሀላፊነት.......................................25

8.17 የአጋርድርጅቶች ........ 25
9 የሰው ሀይል አስተዳደር ........ 25
9.1 ብዛት ........ 25
9.1.1 በጤና ጥበቃ ሚንስቴር ደረጃ፡- ........ 25
9.1.2 በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ፡- ........ 25
9.1.3 በዞን/ ክፍለ ከተማ/ወረዳ ደረጃ፡- ........ 26
9.1.4 በኮማንድ ሴንተር ደረጃ፡- ........ 26
9.1.5 የአምቡላንስ ስምሪት ማዕከል ........ 26
9.2 የአቅም ግንባታ (ሥልጠና) ........ 26
9.3. የማበረታቻ እና የዉሎ አበል አከፋፈል ስርዓትን በተመለከተ ........ 27
9.4 የስነምግባር መርሆች ........ 27
10 የድጋፍ እና ክትትል ሂደት ........ 28
11 የተመረጡ መለኪያዎች ........ 28
11.1 የግብዓት መለኪያዎች ........ 28
11.2 የስራ ሂደት መለኪያዎች ........ 28
11.3 የውጤት መለኪያዎች ........ 29
12. . የኦፕሬሽናል ስታንደርድ መለኪያ ዘዴ ........ 36

# 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሳህራ በታች ከሚገኙ አፍሪካ አገሮች በህዝብ ብዛት ሁለተኛ ደረጃ ስትይዝ 82 ሚሊዮን ከሚደርሰው ህዝቧ 84 በመቶ የሚሆነው በገጠር አካባቢ የሚኖርባት ሲሆን ሀገሪቷም በ9 ክልል እና በ2 ከተማ መስተዳደር የተዋቀረች ናት፡፡የዚህንም ህዝብ የቅድመ ተቋም ጤናን ለመሸፈን የሚያስፈልገው የአምቡላንስ አገልግሎት ሽፋን 1፡100000 ቢሰላ ለጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ 820 አምቡላንሶች ያሥፈልጉታል፡፡ለዚህም የኢትዮጵያ መንግስት አምቡላንሶችን ገዝቶ እያሠራጨ የቅድመ-ሆስፒታልና አምቡላንስ አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እያደረገ ይገኛል፡፡በቀጣይም አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ የምላሽ ግዜን (Emergency Response Time) ለማሻሻልና የአገልግሎት ሽፋኑን 1፡30000-1፡50000 ለማድረስ መንግስት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

የቅድመ-ሆስፒታልና አምቡላንስ ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ማለት የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፤ በመስኩ የሰለጠነ የሰው ሃይል፤ለአገልግሎቱ የሚውሉ ግባቶችን በመጠቀም ለ ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ፈላጊው ህብረተሰብ፤ዓ ሪ ቦታ ትረስ በሙኖትና ሙያዊ ድጋፍ በማትረ□ እስከ ጤና ተቋማት ማድረስ ይሆናል፡፡

የአምቡላንስ አገልግሎት የተጀመረው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ሲሆን በቀጣይም የተለያዩ ሀገራት በተለያየ ጊዜና አጋጣሚ የአምቡላንስ አገልግሎትን በመጀመር በስፋት ሥራ ላይ አውለ□ታል፡፡

ኢትዮጵያም በ1920ዎቹ የአለም ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን ማህበር አባል ለመሆን ጥያቄ አቅርባ በጄኔቭ ኮንቬንሽን 48ኛ ሀገር ሆና ከተመዘገበች በኋላ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር በ1944 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተመስርቶ በነጻ የአምቡላንስ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ እስከ አሁን ድረስ ባለ□ መረጃ መሰረት ማህበሩ አገልግሎቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ በ178 አምቡላንሶችና በ 168 ቅርንጫፎች በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከ2001ዓ/ም ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በጋራ በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የቅድመ ሆስፒታል አምቡላንስ አገልግሎትን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት አገልገሎቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከልና መቆጣጠር ኤጀንሲ በስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስድስት

አምቡላንሶች እንዲጀምር ተደርጓል።በተጨማሪም አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ የሆስፒታሎችና የፖሊስ አምቡላንሶች የጎላ ሚና ሲኖራቸው በግሉ ሴክተርም የጠብታ አምቡላንስ ቅድመ ሆስፒታል ድንገተኛ የህክምና አገልግሎት በአምስት አምቡላንሶች በአንድ ቅርንጫፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ፡፡

ከላይ የተገለጹት አገልግሎቶች እየተሰጡ ቢሆንም በሃገሪቷ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የሕዝብ ብዛት መጨመር፤የከተሞች መስፋፋት፤የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ድንገተኛ አደጋዎች መበራከት፤ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ፍላጎቱን እንዲጨምር አደርጎታል፡፡

በተመሳሳይም በመስራት ላይ የሚገኙት አምቡላንሶች ለተገቢውና ለታቀደላቸው አላማ በትክክል በስራ ላይ ባለመዋላቸው ይህም ለቢሮ ስራ፣ለሰርቪስና ለተለያዩ እቃ ማመላለሻ መዋላቸው፤ የህብረተሰቡ ስለአገልግሎቱና ስለአጠቃቀሙ ግንዛቤ ማነስ ይህም የጥሪውን መስመር ላላስፈላጊ ጥሪ በመጠቀም ተገቢውን አገልግሎት ማዘግየት፤በወረዳዎችና በዞን መካከል ያለው የአምቡላንስ የግንኙነት መረብ አለመጠናከር፤የአምቡላንስ የፋይናንስና በጀት አጠቃቀም ግልጽ አለመሆን፤በወጥነት የሚሰሩበት ዝርዝር መመርያ አለመኖር የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና መሰል ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲያስችል የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማዋቀር ይህ መመሪያ እንዲዘጋጅ አድርጓል፡፡

ይህ መመሪያ በድንገተኛ አደጋ በህመም እና በወሊድ ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን በተደራጀና ወጥነት ባለው የአምቡላንስና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ስርዓት በመዘርጋት ሞትና ጉዳትን ይቀንሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

በ2003 ዓ.ም የሚያሳየው መረጃ የእናቶች ሞት 470/100000 ሲሆን ይህም በ2007 መጨረሻ ለማሳካት ከታቀደው የምእተአመቱ የእድገት ግብ (MDG GOAL) ጋር ሲነጻጸር ብዙ ሊሰራ እንደሚገባው ይጠቁማል፡፡ይሄንንም ከወሊድ ጋር የተያያዘውን የእናቶች ሞት ለመቀነስ እናቶች በምጥ ወይም በህመም ግዜ ወደጤና ተቋማት በአፋጣኝ እንዲደርሱ እና በጤና ተቋም እንዲወልዱ ማድረግ ሊጠቀሱ ከሚችሉት መፍትሄዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ከመኪና አደጋ ጋር በተያያዘም በ2003 ዓ.ም ብቻ በሃገራችን 2581 ሰው ሞቷል፡፡በ2005 የሚያሳየውም የመኪና አደጋ ሞት መረጃም 72/10000 መኪና ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለዚህም ተጠቃሽ ከሚሆኑት ነገሮች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በጣም ውስን መሆኑ፤የተደራጀና ማዕከላዊነት ያለው የጥሪ መቀበያና ስምሪት ማዕከል አለመኖር፤የአምቡላንሶች በተሟላ መሳሪያና በሰለጠነ የሰው ሃይል አለመደራጀት፤እና የመሳሰሉትን በመገንዘብ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የዚህ መመሪያ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## 3. ዓላማ

### 3.1 ዋና ዓላማ

- የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎቱን ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ ለነፍሰጡር እናቶች፤ ለህፃናት፤በድንገተኛ ህመም ለታመሙ ሰዎች እንዲሁም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተጋለጡ ሰዎች ተገቢ የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ በማድረግ በሰው ላይ የሚደርሰውን ህመምና ሞት መቀነስ፡፡

### 3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- ወጥነትና ዘላቂነት ያለው የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ስርዓት ለመዘርጋት

- የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለታለመለት አላማ ብቻ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት ለመዘርጋት
- ለሚደርሱ ጥሪዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት የድንገተኛ ህክምና እርዳታ አሰጣጥን ወደተሻለ ደረጃ ማድረስ
- ማዕከላዊነት ያለው ስምሪት (ኮማንድ ፖስት) መፍጠርና ጠንካራ የእርስ በእርስ የግንኙነት እንዲኖር ማድረግ
- የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ መፍጠር
- በሰለጠኑ ባለሙዎች በመታገዝ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮች ተገቢውን የህክምና ድጋፌ እያደረጉ በፍጥነት ወደ ጤና ተቋማት ለማድረስ የሚቻልበትን አሰራር ስልት መዘርጋት

# 4. ኦፕሬሽናል ስታንደርድ

4.1 በየደረጃው የሚገኙ ሃላፊነት ያለባቸው አካላት፤ የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ

4.2 በሀገር አቀፍ ደረጃ በማዕከላዊነት የድንገተኛ ጥሪ መቀበያ ባለሶስት ዲጅት ስልክ ቁጥር እንዲሁም የተቀናጀ የግንኙነት ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል

4.3 በቂ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲሁም የሥራ ላይ ስልጠና እንዲኖር ማድረግ

4.4 ወደ ጥሪ ማዕከል ለሚደርሱ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና ጥሪዎች ጊዜውን የጠበቀና ተገቢውን ምላሽ መስጠት

4.5 የጥራት ማሻሻያ ፤የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት መዘርጋት


4.6 ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ደረጃውን የጠበቁ የህክምና መሳሪያዎች፣ መገልገያዎች እና መድሃኒቶችን መሟላት

# 5. የመመሪያው ተፈጻሚነት


ይህ መመሪያ በሃገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች እና ክፍለ ከተማዎቸ ለሚገኙ አምቡላንሶች ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 6. መዋቅርና አስተዳደር

<u>ሀ-የወረዳ መዋቅር</u>



## ለ- የከተማ አስተዳደር መዋቅር



6.1 የአምቡላንሱ መቀመጫ ለክልላዊ መንግስታት በወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት በተመረጠ አገልግሎቱን ለመስጠት አመቺ በሆነ ቦታ፤ በአዲስ አበባ እሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር በመረጠው ቦታ ሲሆን ማዘጋጃ ቤት የሚያስተዳድራቸው ከተሞች ላይ ደግሞ ማዘጋጃ ቤቱ ለአገልግሎቱ አመቺ ሆኖ በመረጠው ቦታ ይሆናል፡፡

6.2 የወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት የአምቡላንስ አገልግሎትን እንደ የእለት ተእለት ተግባሩ የሚያከናውን ቡድን ያቋቁማል፣ ቡድኑም ተጠሪነቱ ለጤ/ጥ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ይሆናል፡፡በተጨማሪም በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የበላይ ጠባቂነት ክትትል የሚደረግበት ይሆናል::

6.3 ለአምቡላንስ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የነዳጅና ቅባት፣የጥገና፣ውሎ አበል፣ የመድሃኒት እና የህክምና ቁሳቁስ እንዲሁም ለሌሎች ስራ ማስኬጃ ወጭዎች በጀት የወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት ኃላፊ በወረዳው አስተዳደር እያስወሰነ በአመታዊ የበጀት እቅዱ ውስጥ በማስያዝ ወጪውን ሙሉ በሙሉ የመሸፈን ኃላፊነት መውሰድ ይኖርበታል፡፡

6.4 የአምቡላንሱን ደህንነት በተገቢው ለመጠበቅና ለረጅም ግዜ እንዲያገለግል ለማስቻል የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ መመሪያ በሚያዘው መሰረት ኪሎ ሜትሩና ወቅቱ ተጠብቆ ሰርቪስ እንዲደረግ እና ለዚህም የሚያስፈልገው በጀት በእቅድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

6.5 የአገልግሎት ዘመኑ ከማብቃቱ በፊት አምቡላንሱን በአዲስ በመተካት አገልግሎቱን በዘለቄታዊነት ለማስቀጠል እንዲቻል የወረዳውን ህብረተሰብ በማወያየት ቀጣይነት ያለው መጠነኛ መዋጮ በማውጣት እና የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በማቀድና በመተግበር ገቢውን በዝግ አካውንት ማጠራቀም የሚችልበትን ስልት የወረዳው አሰተዳደር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

6.6 አምቡላንሱ በሁሉም ቀናት የ24 ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ የሚጠበቅ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የተሟላ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል::

6.7 ከስራ ሰዓት ውጭ ተመድበው አገልግሎት ለሚሰጡ የአምቡላብስ ባለሙያዎችና ሹፌር መመሪያን መሰረት ያደረገና ተገቢ የውሎ አበል ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል::


6.8 አምቡላንሱ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችንና መድሃኒቶችን በመያዝ በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መልክ ዝግጁ መሆኑን የወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት ኀላፊ በተከታታይ እና በቋሚነት በቅርብ የሚከታተለው ይሆናል፡፡

6.9 አምቡላንሱ በማንኛውም ሰአት መንቀሳቀስ የሚችለው አገልግሎት እንዲሰጥ ከአምቡላንስ አገልግሎት አስተባባሪው ወይም ተወካዩ የታዘዘበትን እና ማህተም ያረፈበትን መውጫ ወይም የይለፍ ማስረጃ ሲይዝ ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም በሌሊት እና በእረፍት ቀናት ለሚያጋጥሙ ጥሪዎች በነዚህ ጊዜያት በስራ ላይ ያለ ተወካይ አመራር ሊሰጥ ይገባል፡፡

6.10 የአገልግሎት ጥያቄ ከህብረተሰቡ ፣ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ፣ከጤና ጣቢያ ወይም ከሆስፒታል ጥሪ ሲቀርብ ከአምቡላንስ አገልግሎት አስተባባሪው ወይም ተወካዩ እየታዘዘ ጥሪ ወደቀረበበት ስፍራ ተንቀሳቅሶ የሚረዳውን ግለሰብ አገልግሎት እየሰጠ በፍጥነት ወደ ጤና ተቋም ያደርሳል፣ጤና ተቋሙ ተገልጋዩን መረከቡን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም በአምቡላንስ ውስጥ የተሰጠውን የህክምና አገልግሎት እና የአምቡላንስ እንቅስቃሴ በተዘጋጀው ቅጽ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

6.11 የአምቡላንስ አገልግሎት የሚሰጠው በሴክተሩ ያለውን የህሙማን ቅብብሎሽ ስርአት ተከትሎ ሲሆን ይህም ህሙማኑ ከሚገኙበት አገልግሎቱ በቅርብ ወደሚገኝበት የጤና ተቋም ይሆናል፡፡

## 7. የአምቡላንስና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ፍሰት



7.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት በነጻ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የአገልግሎቱም ተጠቃሚዎች የሚከተሉት ናቸው።

7.1.1 ምጥ ላይ ለምትገኝ ነፍሰጡር ሴት

7.1.2 በእርግዝና ላይ ሆና ማንኛውንም አይነት አጣዳፊ ህመም ላይ ለሆነች ሴት

7.1.3 ማናቸውም የህጻናትና የአዋቂ ድንገተኛ እና አጣዳፊ የሆነ ህመም

7.1.4 በተፈጥሮ በመኪና በእሳት ወይም በማናቸውም ሰው ሰራሽ በሆነ አደጋ የሚመጣ የአካል ጉዳት ሲከሰት

7.1.5 ህዝባዊ መድረኮች በሚኖርበት ግዜ እንደ አስፈላጊነቱ የዝግጁነት(standby) አገልግሎት ይሰጣል

7.1.6 ከላይ ከ1-4 ከተጠቀሱት ተገልጋዮች በተጨማሪ አንድ አስታማሚ ብቻ በአምቡላንሱ ውስጥ አብሮ የሚንቀሳቀስ ይሆናል።

7.1.7 ከላይ ከተመለከቱት ጉዳዮች በስተቀር አምቡላንሱ በምንም አይነት መልኩ ለሌሎች ተግባራት መዋል እንደሌለበት የወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት ሙሉ ሃላፊነት በመውሰድ መከታተልና ማረጋገጥ ይኖርበታል።

7.2 የወረዳው ጤ/ጥ/ጽ/ቤት አምቡላንሱ ለታለመለት አላማ በአግባቡ እንዲውል የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለመጨመር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ይኖርበታል።

7.3 የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሰለጠኑ ሁለት ባለሙያዎች በፈረቃ በመመደብ በማንኛውም ግዜ ለ24 ሰአት ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።

7.4 አምቡላንሱን ለማሽከርከር የሚመደበው ሾፌር አምቡላንስ ለማሽከርከር ክህሎት ያለው፤ስለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ግንዛቤ ያለው እና መልካም ስነምግባር የተላበሰ መሆን ይኖርበታል።

7.5 አላስፈላጊ የሆነ የሀብት ብክነትን ለመከላከል ይቻል ዘንድ እያንዳነዱ የአምቡላነስ እንቅስቃሴ በወረዳው የግዢ፣ፋይናንስና ንብረት ደጋፊ የስራ ሂደት አስተባባሪ በተሽከርካሪ ሎግ ቡክ ላይ የተመሰረተ ጥብቅ ክትትል እየተደረገበት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፤የወረዳ ጤ/ጥ/ጽ/ቤት ኃላፊም የአምቡላንስ እንቅስቃሴ በዚሁ አግባብ መከናወኑን በተከታታይነት ክትትል ያደርጋል።

7.6 ከህሙማን እና ቤተሰቦቻቸው ማንኛውንም ክፍያ የሚቀበሉ እና ሌሎች የስነምግባር ግድፈቶች የሚታይባቸው የአምቡላንስ ሾፌሮችና ባለሙያዎች የዲሲፒሊን መመሪያን መሰረት ያደረገ ተመጣጣኝ እርምጃ በቀጥታ የሚወሰድባቸው ይሆናል፡፡

7.7 የአምቡላንስ አገልግሎት ከፍተኛ የስራ ማስኬጃ በጀትን የሚጠይቅ ስለሆነ ማንኛውም የአምቡላንስ አገልግሎትን የሚጠይቅም ሆነ የሚፈቅድ አካል ሀላፊነት በጎደለው መልኩ ከግዴለሽነት እና ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰቦች ከሚመነጩ አፈጻጸሞች የሚከሰት አላስፈላጊ የሀብት ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊወስድ ይገባል፡፡

7.8 በየደረጃው የሚገኙ የጤናው ሴክተር መዋቀር (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ክልል ጤና ቢሮ፣ዞን ጤና መምሪያዎች እና ወረዳ ጤ/ጥ/ጽ/ቤቶች) የዚህን የአምቡላንስ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ አፈጻጸም በተጠናከረ መልኩ የሚከታተሉ እና በየወቅቱም የሚገመግሙ ይሆናል፡፡

# 8. የባለ ድርሻ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት

## 8.1 የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ሀላፊነት

8.1.1 በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ስርዓትን የሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል፤ እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ያደርጋል፡፡

8.1.2 ለወረዳ□ችና ለከተማ አስተዳደሮች አገልግሎት የሚውሉ አምቡላንሶችን ለአንድ ጊዜ ብቻ ገዝቶ ለክልሎች ጸሰራ□ል ፤በቀጣይነትም ወረዳ□ችና ክልሎች በሚያቅርቡት በጀት መሰረት በማእከል ገዝቶ ያቀርባል፡፡

8.1.3 የተጠናከር የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ኬዝቲም በማዋቀር የሀገሪቱን የአንቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ወቅታዊ አፈጻጸም ይገመግማል፤ት□ፋዊ ክትትልም ያደርጋል፡፡

8.1.4 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ዘለቄታዊነትን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ስርዓተ ትምህርት ይቀርፃል፤የአሠልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፡፡

8.1.5 ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመተባበር ለሀገሪቱ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት □ርጽ ጸ□□ል፡፡

8.1.6 ሁሉንም አጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር ለአገልግሎቱ ሀብት በማሰባሰብ ቀጣይነት ያለው የአምቡላንስ አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

8.1.7 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የዕቅድ፤መረጃ አያያዝና ሪፖርት ስርዓትን ይዘረጋል ፤አፈፃጸሙንም ይከታተላል፡፡

8.1.8 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ሀላፊነትና ተጠያቂነትን መሰረት ባደረገ መልኩ የስራ ፍቃድ ይሰጣል፤ይቆጣጠራል የፍቃድ እድሳት ያደርጋል፤ ለክልሎች ውክልና ይሰጣል፡፡

8.1.9 ስለድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል

## 8.2 የክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

8.2.1 በ□ልሉ ለሚሰጠው የአምቡላንስ አገልግሎት ትግበራ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች አስፈላጊውን ዝግጅት□እንዲያደርጉ ሙሉ ሓላፊነት ይወስዳል፤

8.2.2 ለመ□በኛ ወጭዎች በጀት በመመደብ የአምቡላንስ አገልግሎቱ እንዳይቋረዓ ጸ□ር□ል፤

8.2.3 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ያሉት አምቡላንሶች እንዲጠገኑና፣መተካት በሚያስፈልግበት ወቅትም አዲስ በመግዛት እንዲተኩ ያደርጋል፤

8.2.4 አስፈላጊው የሰው ሀይል መመደቡን ያረጋግጣል ፣

8.2.5 አምቡላንሶቹን ለማሰራጨት ከወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ወይም የከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋራ የመግባቢያ ሰነድ ይፈርማል፤

8.2.6 አምቡላንሶቹ የድንገተኛ የሕክምና አገልግሎትን ለመስጠት ብቻ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

8.2.7 የድንገተኛ የሕክምና እርዳታ እና የአምቡላንስ አገልግሎትን ወቅታዊ የሆነ ቁጥጥር እና ግምገማን ያካሂዳል፤እንዳስፈላጊነቱም ተገቢ የሆነ እርምጽ □□ስ□ል፤

8.2.8 አገልግሎቱን በተመለከተ ለውል ሰጪው በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲቀርብ ጸ□ር□ል፤

## 8.3 የክልል ጤና ቢሮዎች ተግባርና ሀላፊነት

8.3.1 የሀገር አቀፍ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መመሪያ በወረዳ□ችና ከተማ አስተዳደሮች እን□ተቹር እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የአፈጻጸም መመሪያ/ደንብ ያወጣል ፤ትግበራውን ይከታተላል፤ይገመግማል፡፡

8.3.2 ለአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መ□በኛ በጀት በመመ□ብ እንዲሁም ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ ለምትክ አምቡላንስ መግዢያ ገቢ የማሰባሰቢያ ስርአት በመቅረጽ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ያደርጋል በወረዳዎች የሚታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፡፡

8.3.3 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን ሙሉ ሀላፊነትና ተጠያቂነትን መሰረት ባደረገ መልኩ በሰነድ አስደግፎ አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት ያስተላልፋል፡፡

8.3.4 በአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ዙሪያ ቀጣይነት ያለው ትምህርትና ስልጠና ለአገልግሎቱ ሰራተኞች በማመቻቸት ተገቢው የሰው ሀይል መመደቡን ያረጋግጣል፡፡

8.3.5 አምቡላንሶቹ ለድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ብቻ መዋላቸውንያረጋግጣል፤ይከታተላል፤ግምገማ ያካሄዳል፤እንዳስፈላጊነቱም በክልሉ በወጣው ደንብ መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጽ □□ስ□ል፡፡

8.3.6 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ከጤና ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራቱን ያረጋግጣል፡፡

8.3.7 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ሀላፊነትና ተጠያቂነትን መሰረት ባደረገ መልኩ የስራ ፍቃድ ይሰጣል ፤ይቆጣጠራል የፍቃድ እድሳት ያደርጋል፡፡

8.3.8 የእቅድ፤ሪፖርትና መረጃ አያያዝ ስርአት በመዘርጋት የአገልግሎቱን መረጃ ያጠናቅራል በየሩብ አመቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

8.3.9 ስለድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል

## 8.4 የዞን ጤና ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት

8.4.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መመርያውን ይከታተላል፤ይገመግማል፤ ለክልል ጤና ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

8.4.2 መደበኛ በጀት በመመደብ እንዲሁም ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ያደርጋል፡፡

8.4.3 በወረዳዎች የሚታዩ ምርጥ ተመክሮዎችን ያስፋፋል፡፡

8.4.4 ስለድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## 8.5 የወረዳ መስተዳድር ተግባርና ሀላፊነት

8.5.1 ለአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የተመደበውን አምቡላንስ ከታለመት አላማ ውጪ እንዳይውል ይቆጣጠራል፤ይከታተላል፤ ተገቢውን በጀት ይይዛል ፡፡

8.5.2 ስለድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## 8.6 የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት

8.6.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መመሪያን በመተግበር የ24 ሰዓት የአምቡላንስ አግልገሎት ስምሪት ይሰጣል፤ ትግበራውንም ይከታተላል፡፡

8.6.2 የተመደበው አምቡላንስ ለስራው ምቹ በሆነ ቦታና በአስቸኳይ ወደስራ የሚንቀሳቀስበት ማእከል ላይ መቀመጡን ያረጋግጣል፡፡

8.6.3 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አመታዊ የበጀትና ዝርዝር የክንውን እቅድ ያዘጋጃል ፤ያጸድቃል፤ የክንውን እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርት ለዞን /ለክልል ጤና ቢሮ ያሳውቃል፡፡

8.6.4 የተመደበው አምቡላንስ ለታለመለት አላማ /ለድንገተኛ አገልገሎት ብቻ እንዲውል ያደርጋል፤ የእለት ከእለት አፈጻጸሙን ይከከታተላል፤ ይመራል ፤ይገመግማል፤እንዳስፈላጊነቱም በክልሉ በወጣው ደንብ መሰረት ተገቢውንእርምጃ □□ስ□ል፡፡

8.6.5 ለአምቡላነስ አገልግሎት የሚያስፈልጉ በቂ የሰው ሀይል ያደራጃል ፤ያስተዳድራል ፡፡

8.6.6 ለአምቡላንስ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማሙላትና ለተሸከርካሪዎች መደበኛ ጥገና እንዲያገኙ በማድረግ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ያደርጋል፡፡

8.6.7 በወረዳው የሚገኙ አካባቢዎችን በዝርዝር በመለየት ዝቅተኛ የአደጋ ጥሪ ምላሽ መስጫ ሰዓትን ያስቀምጣል ፤ይወስናል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

8.6.8 አገልግሎቱን በተመለከተ የሚከታተል ከወረዳው ፅህፈት ቤቶች ከህብረተሰብና ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ አማካሪ ኮሚቴ ያዋቅራል፤ ይመራል፡፡

8.6.9 የወረዳውን ህብረተሰብ አስተባብሮ ገንዘብ በማሰባሰብ፤ ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር፤ በጀት በመመደብና በዝግ አካውንት ለአንቡላንስ እልቂት መተኪያ በማጠራቀም አገልግሎቱ ሳይቋረጥ በግዢ እንዲተኩ ያደርጋል፡፡

8.6.10 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስለአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለማኅበረሰቡ እንዲያስተምሩ ያበረታታል፡፡

## 8.7 የጥሪ መቀበያ ማእከል ሰራተኛ ተግባርና ሀላፊነት

8.7.1 ወደ ማእከሉ የተደረገ ማንኛውንም ድገተኛ ጥሪ ይቀበላል ፣በመለየት፣ይመዘግባል፣ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል ፣የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን ያደራጃል፡፡

8.7.2 በጥሪ መቀቢያ ማእከል ውስጥ ማንኛውንም ጥሪ በጨዋነት ፣በትህትና፣ ሙያን በተላበሰ አኳሓን ያስተናግዳል፡፡

8.7.3 የጥሪ መቀበያ ማእከል ሰራተኛ ጥሪ በተደረገበት ጊዜ ስለተገልጋይ መሰረታዊ መረጃ በመሰብሰብና ድንገተኛ መሆኑን በማረጋገጥ የአምቡላንስ ስምሪት ያደርጋል፡፡

8.7.4 በቅርብ ከሚገኝ ጤና ተቋም ጋር የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ለድንገተኛ አገልግሎት ዝግጁ በሆነ ተቋም እንዲሰማራና ግልጋሎት እንዲያገኝ ያመቻቻል፡፡

8.7.5 ከአምቡላንስ አገልግሎት ጠያቂው ጋር መረጃ በመለዋወጥ የተገልጋዩን ህይወት ለማቆየት የሚያስችል ሙያዊ ምክርና የሀሳብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

8.7.6 የክንውን ሪፖርት በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

## 8.8 የጤና ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት

8.8.1 ተቋሙ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፣በአምቡላንስ የመጣውን ተገልጋይ የመቀበል፣ የማስተናገድ ሀላፊነትና ግዴታ አለበት፣ይህም አስተማሚ የሌላቸውን ተገልጋዬችን ያካትታል ፡፡

8.8.2 በጤና ተቋማት ውስጥ ያሉ የድንገተኛ ክፍል ባለሙያዎች ከ5 ደቂቃ ባነሰ ጊዜ በመቀበል የአምቡላንሱን ቡድኑን ለቀጣዩ ስራ ያሰናብታል፡፡

8.8.3 በድንገተኛ ክፍል ውስጥ ያሉ የጤና ባለሙያዎች ስለተገልጋዩ ከአምቡላንሱ ሰራተኞች የተሞላውን ፎርም ይቀበላሉ፤ ለመቀበላቸውም ይፈርማሉ፡፡

8.8.4 የጤና ተቋሙ የድንገተኛ ክፍል ባለሙያ ተገልጋዩ በአምቡላንስ ጉዞ ላይ እያለ የድንገተኛ ህክምና ባለሙያው ወይም ከማእከል መረጃ ሲጠየቅ ቀናና እውነተኛ መረጃ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

8.8.5 የህክምና ቅብብሎሽ ስርአት በመከተል ከተቋሙ አቅም በላይ ሲሆን ወደ ሌላ ተቋም በጥንቃቄና በፍጥነት ያስተላልፋል፡፡

## 8.9 የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያን ተግባርና ሀላፊነት

8.9.1 ለድንገተኛ ህክምና እርዳታ መስጫ የሚውሉ መሳሪያዎችንና መድሀኒቶች በበቂ ሁኔታ በአምቡላንስ ውስጥ ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆኑን ያረጋገጣል፤እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

8.9.2 የአምቡላንሱን አጠቃላይ የውስጥ ንፅህና ያረጋጣል ፡፡

8.9.3 በማንኛውም ቦታና ሁኔታ ሙያው የሚጠይቀውን ስነምግባርና የህመምተኛውን መብት በመጠበቅ ተገቢውን አገልግሎት ይሰጣል፡፡

8.9.4 የእራሱን፤ የስራ አጋሮቹንና የተገልጋዩን ደህንነት ያረጋግጣል፡፡

8.9.5 የታማሚውን አጠቃላይ ሁኔታ በመረዳት አስፋላጊውን የህክምና እርዳታ ይሰጣል፡፡

8.9.6 የተገልጋይ መረጃዎችን በመቀበል ቅድሚያ ለሚያስፈልገው የህክምና እርዳታ ይሰጣል፡፡

8.9.7 የድናገተኛ ህክምና ባለሙያ ከጤና ተቋማትና ከጥሪ ማእከሉ ጋር ስለያዘው ተገልጋይ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፡፡

8.9.8 ተረጂውን ከአምቡላንስ በማውጣትና በማውረድ ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ለድንገተኛ ህክምና መስጫ ክፍል ለቀጣይ እርዳታ ያስተላልፋል፡፡

8.9.9 ከተገልጋዩ የተቀበለውን መረጃና ለተረጂው የሰጠውን እርዳታ ለራሱና ለጤና ተቋሙ መዝግቦ ይይዛል፤ በሰነድ አስፈርሞ ያስተላልፋል፡፡

## 8.10 የአንቡላንስ ሹፌር ተግባርና ሀላፊነት

8.10.1 ሁልጊዜ አምቡላንሱን ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑንና የአንቡላንሱን ደህንነት በማረጋገጥ በማንኛውም የጥሪ ወቅት ከአንድ ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ለጉዞ ዝግጁ ያደርጋል።

8.10.2 ከድንገተኛ ህክምና ሰጪ ባለሙያዎች/ቡድን ጋር በትብብር ይሰራል፤ በቡድን መሪው አመራር መሰረት ስራውን ያከናውናል።

8.10.3 አማራጭና አቋራጭ መንገዶችን በመምረጥ በተገቢው ፍጥነት ይጓዛል።

8.10.4 አምቡላንሱ ለተመረጡ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ብቻ እንዲውል ያደርጋል።

8.10.5 የተገልጋዩ አንድ አስታማሚ ብቻ መጫኑን ያረጋግጠል።

## 8.11 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙዎች ተግባርና ሀላፊነት

8.11.1 ከአገልግሎት ፈላጊ በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሰረት ለድንገተኛ አገልግሎት ማእከል ጥሪ በማድረግ እርዳታ ፈላጊውን ያግዛሉ፤ያስተባብራሉ፤የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ይሰጣሉ።

8.11.2 ህብረተሰቡ የድንገተኛ ጥሪ ማእከል ስልክን ለድንገተኛ እርዳታ ጥሪ ብቻ ማዋል እነዳለበት ያሳውቃሉ፤ ስለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ምንነት ያስተምራሉ።

## 8.12 የህብረተሰቡ ተግባርና ሀላፊነት

8.12.1 የአምቡላንስ አገልግሎት ከታለመለት አላማ ውጭ ለግል ጥቅም ሲውል ካየ ወይም ከሰማ ተገቢ እንዳልሆነ ያስረዳል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

8.12.2 የአምቡላንስና ድንገተኛ አገልግሎት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ በሚደረግ የገቢ ማሰባሰቢያና መዋጮዎች ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል።

8.12.3 የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እነደመሆኑ መጠን ተደራሽነቱን ለማስፋት ጠቃሚ ሀሳቦችን ያቀርባል፤ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ይከታተላል፤

ይገመግማል፤ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፤በአደጋ ጊዜ ተገቢውን ትብብር ያደርጋል፡፡

8.12.4 አምቡላንስና ባለሙያዎች በድንገተኛ ተጠርተው ለስራ ሲንቀሳቀሱ ህብረተሰቡ በተሽከርካሪውም ሆነ በሰራተኞች ላይ አላስፋላጊ ድርጊት ከመፈም መቆጠብ ይኖርበታል ፤ድርጊቱ የሚፈጽሙ ቢኖሩ ለህግ አካላት ያሳውቃሉ፡፡

8.12.5 የድንገተኛ ጥሪ ማእከል ስልክን ለድንገተኛ እርዳታ ጥሪ ብቻ ይጠቀማል፤ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በውይይት፤ በመማማር ለመፍታት ጥረት ያደረጋል፡፡

8.12.6 አሽከርካሪዎች ለአምቡላንስ አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት እንዲችሉ ያስተባብራል፤ ትብብር ያድርጋል ፡፡

8.12.7 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና ባለሙያዎች በድንገተኛ ጥሪ ተጠርተው ለስራ ሲንቀሳቀሱ ህብረተሰቡ በተሽከርካሪውም ሆነ በሰራተኛው ላይ አላስፈላጊ ድርጊቶች ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርበታል፤ድርጊቱን የሚፈጽሙ ቢኖሩ ለህግ አካል ያሳውቃል፡፡

## 8.13 የፖሊስ ተግባርና ሀላፊነት

8.13.1 ፖሊስ ከድንገተኛ ህክምና ማእክል ጥሪ ሲደርሰው አደጋው ወደ ደረሰበት ቦታ በመንቀሳቀስ የአምቡላንስ አገልግሎት ቡድኑን የስራ እንቅስቃሴ ያመቻቻል ፤ያግዛል፡፡

8.13.2 የተገልጋዩን ንብረትና ደህንነት ይጠብቃል ፡፡

8.13.3 ማናቸውንም የድንገተኛ አደጋ በሚያጋጥማቸው ወቅት ለአምቡላንስና ድንገተኛ አገልግሎት ማእከል በማሳወቅ የተቀላጠፈ ዕርዳታ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

## 8.14 የትራፊክ ፖሊስ ተግባርና ሀላፊነት

8.14.1 አምቡላንሶች ለድንገተኛ እርዳታ አገልግሎት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የትራፊክ ቅድሚያ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ለአምቡላንስ

ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ የማይሰጡ አሽከርካሪዎችን ለህግ ያቀርባል፡፡

8.14.2 ማናቸውንም የድንገተኛ አደጋ በሚያጋጥማቸው ወቅት ለአምቡላንስና ድንገተኛ አገልግሎት ማእከል በማሳወቅ የተቀላጠፈ ዕርዳታ እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡

## 8.15 የኢትዮጲያ ቀይ መስቀል ማህበር ተግባርና ሀላፊነት

8.15.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መመሪያን ይተገብራል፤የራሱን የአምቡላንስ አስተዳደር መመሪያ መሰረታዊ መርሆዎቹን መሰረት በማድረግና ከአገር አቀፉ መመሪያ ጋር በማጣጣም ያወጣል፡፡

8.15.2 ከክልል ፤ከዞን፤ ከወረዳና ከከተማ መስተዳድሮች ጋር ያሉትን ስምምነቶች ያድሳል፤አስተዳደራዊ አገልግሎቱን ያጠናክራል፤ከእነዚህ አካላት በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት አዳዲስ አምቡላንሶችን በመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል፡፡

8.15.3 ከክልል መስተዳደሮች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሰረት የመንግስት የአምቡላንስ ተሽከርካሪዎችን በመረከብ ሊያስተዳድር ይችላል፡፡ነገር ግን የንብረት ባለቤትንት መብት በመንግስት መለያ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

8.15.4 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አመታዊ የበጀትና ዝርዝር የክንውን እቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤የክንውን እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርት ለወረዳ፤ለዞን ፤ለክልል መስተዳድር ያቀርባል፡፡

8.15.5 የጥሪ ማእከሉን ከዋና የመንግስት የጥሪ ማእከል ጋር በማገናኘት አገልግሎቱን ከአንድ ማእከል እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

8.15.6 የመንግስት የዘርፉ አጋር በመሆን አገልግሎትን ያጠናክራል ፤አዳዲስና የተሻሉ አሰራሮችን በማጥናት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

8.15.7 በሰራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የመፍትሄ አቅጣጫ ይቀይሳል ፡፡

### 8.16 የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ኤጀንሲ ተግባርና ሀላፊነት

8.16.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መመሪያን ይተገብራል፡፡

8.16.2 የጥሪ ማእከሉን ከዋና የመንግስት የጥሪ ማእከል ጋር በማገናኘት አገልግሎቱን ከአንድ ማእከል እንዲሰጥ ያደርጋ፡፡

8.16.3 አሁን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በእቅድና በጥናት ያስፋፋል ያጠናክራል ፤አዳዲስና የተሻሉ አሰራሮችን በማጥናት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያቀርባል ፡፡

8.16.4 በሰራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የመፍትሄ አቅጣጫ ይቀይሳል ፡፡

### 8.17 የአጋርድርጅቶች

8.17.1 የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን ለማጠናከር በተለያየ ዘርፍ ያሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሁሉ እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን የስራ ትብብርና እገዛ ያደርጋሉ፡፡

## 9. የሰው ሀይል አስተዳደር

### 9.1 ብዛት

#### 9.1.1 በጤና ጥበቃ ሚንስቴር ደረጃ፡-

9.1.1.1 **ስያሜ፡-** በአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ቡድን ውስጥ የቡድን አስተባበሪው የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አስተባባሪ ሲባል ሌሎቹ የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ኦፊሰር ይባላሉ

#### 9.1.2 በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ፡-

9.1.2.1 **ስያሜ፡-** በአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ቡድን ውስጥ የቡድን አስተባበሪው የአምቡላንስ እና

የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አስተባባሪ ሲባል ሌሎቹ የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ ይባላሉ

### 9.1.3 በዞን/ ክፍለ ከተማ/ወረዳ ደረጃ፡-

9.1.3.1 **ስያሜ፡-** በአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ቡድን ውስጥ የቡድን አስተባበሪው የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አስተባባሪ ሲባል ሌሎቹ የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ ይባላሉ፡፡

### 9.1.4 በኮማንድ ሴንተር ደረጃ፡-

9.1.4.1 **ስያሜ፡-** በአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ቡድን ውስጥ አባላቶቹ ባለው የክልሉ የስራ መዋቅር ተቀናጅተው ሲሰሩ የቡድን አስተባበሪው የአንቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አስተባባሪ ሲባል ሌሎቹ የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ ይባላሉ፡፡

### 9.1.5 የአንቡላነስ ስምሪት ማዕከል

9.1.5.1 **ስያሜ፡-** በአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ቡድን ውስጥ አባላቶቹ የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያን (EMT) ሲሆኑ የቡድን አስተባበሪው የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አስተባባሪ ሲባል ሌሎቹ የአምቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ ይባላሉ፡፡

## 9.2 የአቅም ግንባታ (ሥልጠና)

በየጊዜው በሚካሄዱ ግምገማዊ መድረኮች የሚለዩ የአመለካከት፣የክህሎት፣የግብዓትና የአመራር ስርዓት ማነቆዎችን መፍታት የሰራተኞችን የአፈጻጸም ብቃት ለማሻሻል ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ሥለዚህ በተለያዩ መድረኮች ለሚለዩ የክህሎት ማነቆዎች ተከታታይነት ያለው የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎች በማዘጋጀት ይሰጣል፡፡

## 9.3 የማበረታቻ እና የዉሎ አበል አከፋፈል ስርዓትን በተመለከተ

9.3.1 በሲቪል ሰርቪስ ሚንስቴር አንድ ሲቪል ሰራተኛ በአንድ ቀን ውስጥ መስራት ከሚገባው በላይ ከሰራ የሰራው ትርፍ ሰዓት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው እንደሚገባ

9.3.2 አዲስ የደመወዝ ስኬል እየተጠና ሲሆን በዛ መሰረት ተፈጻሚ የሚደረግ መሆኑ ታሳቢ ቢደረግ

9.3.3 ለድንገተኛ አገልግሎት ህክምና ባለሙያዎች ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበአላት በትርፍ ሰአት ክፍያ የሚታሰብ ይሆናል

## 9.4 የስነምግባር መርሆች

9.4.1 ማንኛውም የድንገተኛ አምቡላንስ ባለሙያ ባለው እውቀት እና ልምድ እንዲሁም ሙያውን በሚፈቅድለት ደረጃ ስራውን ማከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

9.4.2 ማንኛውም እራሱን የሚያውቅ እና በራሱ መወሰንን የሚችል ታማሚ ካለ ፍቃድ ማጓጓዝም ሆነ ሌሎች ህክምናዎችን አገልግሎቶች ማድረግ የለበትም ሆኖም ግን የእርዳታውን አስፈላጊነት እና እርዳታው ባይደረግ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

9.4.3 የሚሰጡ ማናቸውም እርዳታዎች በዓለም አቀፍ ህግ የተቀመጡ የታካሚ መብቶችን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

9.4.4 ህጻናት፣ የከፋ ጉዳት እንዲሁም ህመም የደረሰባቸው፣ የአእምሮ ጉድለት ያጋጠማቸውን ታማሚዎች የህሙማኑን ፈቃድ ሳይጠይቅ ተገቢውን እርዳታ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

9.4.5 ማንኛውም የድንገተኛ ህክምና ባለሙያ የታካሚውን የህክምና ምስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ያለታካሚው ፍቃድ መረጃውን ለሌላ ወገን ማሳወቅ የለበትም፡፡ሆኖም ግን በማህበረሰቡ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ከግምት በማስገባት ምስጢሩ ይፋ ሊሆን ይቻላል፡፡

9.4.6 ማንኛውም የድንገተኛ ህክምና እገልግሎት ባለሙያ ሁልጊዜ ለየትኛውም ወገን ሳያዳላ ገለልተኛ ሆኖ ስራውን ማከናወን አለበት፡፡

9.4.7 የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ባለሙያ ስራውን ከስጋት ነጻ በሆነ መንገድ እንዲያከናውን ማድረግ ተገቢ ሲሆን ስጋት በሚፈጥሩ ሁኔታዎች አስፈላጊውን እርዳታ እንዲሰጥ ከማድረግ መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡

9.4.8 ለሚፈጠሩ ማናቸውም የዲሲፕሊን ጉድለቶች በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ቅጣቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# 10. የድጋፍ እና ክትትል ሂደት

10.1 የአምቡላንስ አገልግሎት ድጋፍ እና ክትትል በሚከተሉት ዝርዝር መለኪያዎች መሰረት ሊደረግ ይችላል፡፡

10.2 ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስደስት ወር እና ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ማቅረብ

10.3 ቀጣይነት ያለው በየሩብ ዓመት ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ እና ሪፖርት ማዘጋጀት

10.4 በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ላይ በተመረጡ መለኪያዎች መሰረት የአንቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና የአፈጻጸም ደረጃ ማቅረብ

10.5 የመረጃ አያያዝ ስርዓት መዘርጋት

# 11. የተመረጡ መለኪያዎች

## 11.1 የግብዓት መለኪያዎች

11.1.1 በመስራት ላይ የሚገኙ የስልክ እና የሬድዮ መስመሮች ብዛት

11.1.2 በመስራት ላይ የሚገኙ አንቡላንሶች ብዛት/በመቶኛ

## 11.2 የስራ ሂደት መለኪያዎች

11.2.1 ከተደረጉ ጥሪዎች ውስጥ የአንቡላንስ አገልግሎት ያገኙ በመቶኛ

11.2.2 አንቡላንስ ካገኙ ድንገተኛ ጥሪዎች ውስጥ ተገልጋዩ ጋር ለመድረስ በአማካይ የወሰደው ጊዜ (Emergency response time)

## 11.3 የውጤት መለኪያዎች

11.3.1 የአንቡላንስ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ቁጥር በመቶኛ

11.3.2 ከተገልጋይ እርካታ የተሰበሰቡ መረጃዎች (በቀጣይ በሚዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት)

አባሪ፡- የምዝገባና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾች

1. <u>**የአንቡላንስ ጥሪ መቀበያ ቅጽ**</u>/ባህር መዝገብ/ 1

| ቀን | የጥሪ ሰአት | የደዋይ ስም | የደዋይ ስልክ | የተገልጋይ/ተጎጂ ጾታና እድሜ | ልዩ ቦታ /የአካባቢው መታወቂያ ስም/ | የችግሩ አይነት(√) | | | | | | | አምቡላንስ የተንቀሳቀሰበት ሰአት | አምቡላንሱ ቦታው ላይ የደረሰበት ሰአት | አምቡላንሱ ቦታው ላይ ለመድረስ የወሰደበት ሰአት/ በደቂቃ /በሰአት | አምቡላንሱ ጤናተቋም የደረሰበት ሰአት | የተቀበለው ጤና ተቋም ስም | የተጠቀመው ኪሎሜትር | አምቡላንሱ ያልተሰማራበት ምክንያት (አገልግሎት ያልሰጠበት ምክኒያት) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ወላድ/የእርግዝና | የመኪና አደጋ | የመውደቅ አደጋ | ትብትብ | በዓ□ት□ተ□□ | አጣዳፊ ህመም | ሌሎች/ይጻፍ | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

## 2 የአንቡላንስ መዘዋወሪያ ቅጽ 2

i. የአምቡላንስ ጥሪ የደረሰበት ሰዓት_________
ii. አገልግሎት ለማግኘት የደወለው ስምና ስልክ _________
iii. ሳይረን የተደረገበት ሰአት_________ አንቡላንስ ከማሰራጫ የወጣበት ሰአት_________
iv. አገልግሎቱ ተሰጠበት ቀን_________ ክፍለ ከተማ/ዞን _________ ወረዳ_________ልዩ ቦታ_________
v. አገልግሎት የተደረገለት ሰው ስም_________ ጸታ_________ ዕድሜ_________
vi. አገልግሎት ፈላጊው ጋር ለመድረስ የፈጀበት ሰዓት_________ ታካሚውን ጤና ተቋም ለማድረስ የወሰደው ጊዜ_________
vii. የህመሙ/የአደጋው ዓይነት_________የተወሰደበት ጤና ተቋም_________
viii. ወደ ክፍላቸው የተመለሱበት ጊዜ_________ የተሰማራ ባለሙያ ብዛትና ስም_________
ix. የነዳጅ ፍጆታ መጠን በሊትር_________ የተጠቀመው ኪሎሜትር_________
x. በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ያጋጠመ ችግር________________________________________
xi. አገልግሎቱ የተሰጠበት ቅርንጫፍ_________

የሹፌሩ ስም_________

ፊርማ _________

## ወርሃዊ የኮማንድ ሴንተር/የወረዳ/ጤና ቢሮ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

| የወረዳው ስም | የህመሙ/የአደጋው ዓይነት | | | | | | | አማካይ ተገልጋዩ ጋር የተደረሰበት ጊዜ በደቂቃ | | | እድሜ | | ጥሪ የተደረገበት ቦታ(ጤና ተቋም፣ከማኅበረሰቡ) | | | | | ከጠቅላላው ጥሪ | | | ያልተስተናገደበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 5-10 | 10-20 | 20ና ከ20 በላይ | ከ5 በታች | 5 እና ከ5 በላይ | ህብረተሰቡ | | ጤና ጣብያ | ሆስፒታል | የግል ጤና ተቋም | የተስተናገደ | ያልተስተናገደ | ድምር | |
| | | | | | | | | | | | | | ከቤት | ከሌሎች | | | | | | | |
| | ወላድ/የእርግዝና ህመም | የመኪና አደጋ | የመውደቅ አደጋ | በዓ□ት□ተ□□ | ትብትብ | አጣዳፊ ህመም | ሌሎች/ይጻፍ | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

**EMS- Ambulance patient care form**

<table>
<tr><td colspan="2">Name ________________________________________<br><br>Age_______ Sex_____</td><td colspan="2">Attendant Name:</td><td>Call #</td></tr>
<tr><td colspan="4">Scene Location: Home ☐ Industry☐ Road☐ Work place ☐ From health facility ☐<br>Other ☐</td><td>Phone</td></tr>
<tr><td>Region</td><td>Town</td><td colspan="2">Zone/sub city/Woreda</td><td>Kebele/h.no</td></tr>
<tr><td rowspan="2">Dispatch Time:</td><td rowspan="2">Arrive scene Time:</td><td rowspan="2">Scene Leave Time:</td><td>Destination Arrive Time:</td><td>Total trip time:</td></tr>
<tr><td></td><td>Total trip distance:</td></tr>
<tr><td colspan="5">Nature of case Trauma ☐ Medical ☐ OBS/delivery ☐ Pediatric ☐ Psychiatric ☐ Other ☐</td></tr>
<tr><td colspan="5">Type of trauma: RTI ☐ Fall down ☐ Fighting ☐ Gun shot ☐ Stab ☐ Other ☐</td></tr>
<tr><td colspan="5">Medical: Chest pain ☐ Respiratory problems ☐ GIT ☐ Loss of consiousness ☐</td></tr>
</table>

| | |
|---|---|
| **Scene survey**<br><br>Type of incidence ________________________________<br><br>_______________________________________________<br><br>Number of causalities______________<br><br>**Primary assessment**<br><br>**Causality responsiveness**<br><br>***Airway***<br><br>↑ Clear______________<br><br>↑ Partly blocked ____<br><br>↑ Completely blocked _____<br><br>**C –collar** Yes________ No _______<br><br>**Oro-pharyngeal airway** Yes _______ No ________<br><br>**Naso-pharyngeal airway** Yes _______ No ________<br><br>***Breathing***<br><br>↑ Yes___ Effective______ Ineffective____<br><br>↑ No breathing _____________<br><br>**O2 via nasal pronge** Yes_______ No _________<br><br>**O2 with face mask** Yes_______ No_________<br><br>**Assist ventilation** Yes_______ No ________ | **Secondary assessment**<br><br>History<br><br>Symptoms_________________________________________<br>_________________________________________________<br><br>Allergies _______________________________________<br>_________________________________________________<br><br>Medication _______________________________________<br>_________________________________________________<br><br>Past medical history _________________________________<br>_________________________________________________<br>Last meal_________________________________________<br>Events leading to incident_____________________________<br>_________________________________________________<br><br>**Vital signs**<br><br>Time taken _____, ____, ______,<br><br>AVPU Response _____, _____, ______<br><br>Breathing rate _____, _______, ____<br><br>Breathing depth _____, ______, _____<br><br>Pulse rate _____, ______, _____<br><br>Pulse rhythm _____ ,______, _____<br><br>Blood Pressure _______, _______,______<br><br>Skin colure/temp ____,_______,______ |

| *Circulation* | **Head to toe examination/Expose** |
|---|---|
| Carotid Pulse: Yes____ No______ | Head ________________________________________ |
| Peripheral. Pulse Yes____ No ______ | Neck _______________________________________ |
| **CPR** Yes_________ No___________ | Collar bones_________________________________ |
| **IV secured** Yes ________No __________ | Shoulder/,arms___________________________________ |
| **Type of fluid and rate** __________________________ | Chest and back_________________________________ |
| **Bleeding control** Yes ________No___________ | Abdomen and back ______________________________ |
| Severe bleeding ↑ Yes _____ no_______ | Pelvis and buttocks__________________________________ |
| ***Disability***: | Legs/feet__________________________________________ |
| A-alert…………………… | **TREATMENT** ____________________________ |
| V- Responsive to verbal ……….. | |
| P-responsive to pain……………. | **Condition of pt during hand over** |
| U-unresponsive…………………. | Hand over to medical institution |
| Blood glucose level ……………………………… | ↑ Stable↑ ☐ Unstable ↑☐ Dead ☐ |
| Dextrose given ……………………………………… | Time____________________ |
| **Other specify** | Receiving personnel name _______________________ |
| | Signature ……………………………. |
| | Ambulance attendant name ……………………………. |
| | Signature …………………………………… |

## 2. .የኦፕሬሽናል ስታንደርድ መለኪያ ዘዴ

| ተ.ቁ | ኦፕሬሽናል ስታንደርድ | የመለኪያ ዘዴ | ስታንዳርዱ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ተሟልቷል | አልተሟላም | |
| 1 | በየደረጃው የሚገኙ ሃላፊነት ያለባቸው አካላት፤ የህብረተሱን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲረጋጋጥ ማድረግ አለባቸው | ወርሃዊ ግንዛቤ ማስጨበጫ( በሚዲያ፡ መድረክ፡ ብሮሸር)<br>• የህብረተሰብ ተሳትፎ ( አገልግሎት ተጠቃሚነትና ቀጣይነት)<br>• ሪፖርት | | | |
| 2 | በሀገር አቀፍ ደረጃ ተማሳሳይ የድንገተኛ ጥሪ መቀበያ ቁጥር (ባለሶስት ዲጅት) እንዲሁም የተቀናጀ የግንኙነት ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል፡፡ | • ማዕከላዊነት ያለው ስምሪት (ኮማንድ ፖስት) መኖር<br>• የቅርንጫፍ ስምሪት( disepach center)<br>• ባለሶስት ዲጅት ስልክ /ራድዮ/ማስማርስልክ/<br>• የተቀናጃ ግንኙነትና አሰራር | | | |
| 3 | በቂ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እነዲሁም የሥራ ላይ ስልጠና እንዲኖር ማድረግ | • የተሟላ የሰው ሃይል ቁጥር<br>• የስራ ላይ ስልጠና ብዛት | | | |
| 4 | ወደ ጥሪ ማዕከል ለሚደርሱ የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና ጥሪዎች ጊዜውን የጠበቀና ተገቢውን ምላሽ መስጠት | (ለከተሞች)<br>• በአማካይ ለአጭር እርቀት እስከ 3 ኪ.ሜ በ 5 ደቂቃ፤<br>• ለመካከለኛ እርቀት በአማካይ 6 ኪ.ሜ በ8 ደቂቃ ፤ ለረጅም እርቀት በአማካይ 14 ኪ.ሜ በ15 ደቂቃዎች<br>(ከከተማ ውጭ)<br>• እንደመንገዱ አይነትና እርቀት የሚለያይ ይሆናል | | | |
| 5 | የጥራት ማሻሻያ ፤የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት መዘርጋትና መካታታል | • ወራዊ የድጋፍና ክትትል ክንዊኖች ብዛት<br>• በየግማሽ አመቱ የስራ አፈፃፃም ግምገማ<br>• የተሰጡ አምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች ብዛት<br>o በአይነት__________________<br>o በመጠን____________________ | | | |
| 6 | ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ የህክምና መሳሪዎች፤ መጋልገያዎችና መድሃኒቶች መያዝ ይኖርባቸዋል | • የሚሰራ አምቡላንስ ብዛት<br>• የህክምና መሳሪዎች፤ መጋልገያዎችና መድሃኒቶች ሁኔታ፡፡ | | | |